# መራር እውነቶች

እውነቱ ዘለቀ 11-21-14

አዲስ አድማስ ጋዜጣ ጥቅምት 22/2007 ዓ.ም በወጣው እትሙ የወቅቱን የመድረክ ሊቀመንበር ዶ/ር መረራ ጉዲናን ቃለመጠይቅ አድርጎላቸው ነበር፡፡ ዶ/ር መረራ ጉዲና በአሜሪካን ሀገር ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ ጥናት እንዲያካሂዱ ጠይቆአቸው በዚህም መሰረት በአሜሪካ ለ6 ወራት መቆየታቸውን "የኢትዮጵያ ዲያስፖራ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚደረገው ዴሞክራሲያዊ ትግል ውስጥ ያለው ሚና" የሚለውን አጥንተው ሪፖርቱን እንዳቀረቡ ገልፀዋል፡፡

በስድስት ወራት ቆይታቸው የተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር በኢትዮጵያ ጉዳይ "ያገባኛል" የሚሉ የዳያስፖራ ተቃዋሚዎችን እንዳነጋገሩ ዶ/ር መረራ ተናግረዋል፡፡ ዶ/ር መረራ "የኢትዮጵያን ፖለቲካ እንዲሰደድ ያደረገው ገዢው ፓርቲ ነው፤ ጨኸቱንም ቢሆን እዚህ አገር ቤት ብንጯጯህ ይሻላል" ይላሉ፡፡ ዶ/ር መረራ ጉዲና ዋሽንግተን ዲሲ የኢትዮጵያ ሁለተኛ ከተማ እስከመባል መድረስዋን፣ ኢትዮጵያውያኖች ይገኙበታል በተባለበት አካባቢ፤ ሲያትል፣ ሳንዲያጎ፣ ላስቬጋስ፣ ሳንፍራሲስኮ፣ ሚኒሶታ፣ ዳላስ፣ ፊላደልፊያ፣ በመሳሰሉት የአሜሪካ ከተሞች ተዟዙረው "ፖለቲካው ያገባናል" የሚሉትን ማነጋገራቸውንም አስታውሰዋል፡፡

ዶ/ር መረራ በዚያውም ለፓርቲያቸው ድጋፍ ለማሰባሰብ መሞከራቸውን፣ ከሞላጎደል በውጭ ያለው ዲያስፖራ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ያለውን ስሜት አዳምጫለሁ ባይ ናቸው፤ ዶ/ር መረራ። በኢሳት፣ በቪኦኤ፣ በኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ የኢትዮጵያን ፓለቲካ በተመለከተ በስፋት ቃለምልልስ ክርክሮችን ለማድረግ መሞከራቸውንም ተናግረዋል፡፡ በመጨረሻም አሜሪካውያንና ኢትዮጵያውያን በተገኙበት መድረክ ላይ የጥናት ውጤቱን ማቅረባቸውን፣ መሰረታዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት ከኢትዮጵያ መንግስት በውጭው ዓለም ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ምን ይጠበቃል በሚል ሶስት መሰረታዊ ነገሮች ላይ አስታያየት ማቅረባቸውን ይገልፃሉ፡፡

በወቅቱ ፕሬዝዳንት ኦባማ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎችን ሰብስቦ ሲያነጋግር፣ እኔ ጥናት ያቀረብኩበት ዴሞክራቶች የሚመሩት ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት እንዲሁም ዊልሰን ሴንተርና ፍሪደም ሴንተር የሚባሉ ተቋማት በጋራ የአፍሪካ ሲቪል ማህበረሰብ አባላትን ሰብስበው ነበር፡፡ በዚህ መድረክ ላይ ስለአፍሪካ መሰረታዊ ችግሮች ማለትም ስለምርጫና ስለፍትህ፣ ስለሰብዓዊ መብት አከባበር ሀሳቦች ተንፀባርቀው ውይይት ተደርጓል፡፡ በዚህም ስብሰባ ላይ በተናጋሪነት ተሳትፌያለሁ ሲሉ የ6 ወራት ቆይታና ስራቸውን ተናግረዋል፡፡

ዶ/ር መረራ በዴሞክራሲና የኢትዮጵያ ዲያስፖራ በሀገር ውስጡ ትግል ያለውን ሚና ጥናት እንዲያደርጉበት የጋበዛቸው የአሜሪካው ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ የሚሰራውም ሆነ የሚንቀሳቀሰው ከአሜሪካን ብሔራዊ ጥቅም አንፃር ብቻ መሆኑ የታወቃል። ጥናቱን የፈለገው በኢትዮጵያ ዴሞክራሲን ለማስፈን ተጨንቆና ተጠቦ አይደለም። በዋናነት በአብዛኛው የአሜሪካ ዜገነት ባለው ዲያስፖራ አማካኝነት የአሜሪካንን ጥቅም ለማስከበር የሚችል ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚን ወደ ፖለቲካ ስልጣን ለማብቃት የሚያስችል መንገድ ፍለጋ ነው።

ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ በበርካታ የዓለማችን ሀገራት ከብሔራዊ ምርጫዎች ጋር በተያያዘ ምርጫ ሲደርስ ለተቃዋሚውም ከጀርባ በተለያዩ መልኩ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍና እገዛ እያደረገ በውድድሩ ወቅት የኒዮሊበራል ሃይሎች አጀንዳ አሸናፊ ሁኖ እንዲወጣና የፖለቲካ ስልጣን እንዲይዙ ለማድረግ የሚሰራ ተቋም ነው፡፡ በዓለማችን በተለያዩ ግዜያት ከተካሄዱት የቀለም አብዮቶች ጀርባ በዋና ዕቅድ አውጪነት ሲሰራ መቆየቱም ይታወቃል። ይህ ተቋም በተለይ በምስራቅ አውሮፓ ሃገራት ተቃዋሚውን በአይዞህ ባይነት የአደባባይ የተቃውሞ ሰልፎች እንዲጠራ፤ ሰልፈኞቹ በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ወይንም መሪ የፖለቲካ ስልጣኑን ካለቀቀ ወደ ቤታችን አንመለስም በማለት የትራፊክ ስረአትን በማዛባት ሁከት እንዲቀሰቀሱ፣ የሃገረ ንብረት እንዲወድምና የሰው ሕይወት እነዲጠፋ በማደረግ ረገድ ሁነኛ ተዋናይ ነው፡፡

ይህንንም ተከትለው ምዕራባውያን መንግስታት “የሕዝቡን ትግል እንደግፋለን፣ ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ይልቀቅ፤ ይህ ካልሆነ እርዳታ አንሰጥም . . .” እያሉ

ብሔራዊ ውጥረቱንና ቀውሱን ያራግባሉ። ይህን የሚያደርጉት ለዚያ ሃገር ሕዝብ ጥቅም ሳይሆን የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ዓላማ ነው።

ለዚህ ዓላማ በየሀገራቱ ኢትዮጵያንም ጨምሮ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን፣ የሲቪል ሶሳይቲ ተወካዮችን፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ማህበራትን፣ የግሉን ፕሬስ ጋዜጠኞች በራሳቸው ስር በማቀፍ፣ በሀገር ውስጥና በጭ እየወሰዱ አጫጭር ስልጠናዎችን ይሰጣሉ፡፡ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ እያንዳንዱ በያለበትና በተሰማራበት መስክ ወደ ሕዝቡ በመውረድና ግንኙነቱን በማጠናከር ሰፊ ፀረ መንግስት ውዥንብሮችን በመንዛት በምርጫ ወቅት የተደራጀና ጠንካራ ተቃውሞ እንዲያሰማ ያደርጋሉ፡፡ መሪዎችና አስተማሪዎቹም ከፍተኛ ክፍያ ይሰጣቸዋል፡፡

ይኸው የምርጫ ወቅት ተቃውሞ ከቁጥጥር ውጭ እነዲሆን ወደ ትምህርት ቤቶች፣ የመንግስት ተቋማት፣ የትራንስፖርት አገልግሎትና ፋብሪካካዎች እንዲዛመት በማደረግ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴን ያስተጓጉላሉ፡፡ ይሄንኑ ድርጊት በማቀነባበር የሀገር ቤቱንና የውጪውን የዳያስፖራ ተቃዋሚ በመሳሪያነት የሚጠቀመው የኒዮሊበራል ሃይል በናሽናል ኢንዶውመንትፎር ፎር ዴሞክራሲ በተሰኘው ተቋም አማካኝነት በምእራቡ ዓለም ታላላቅ ሚዲያዎች “የሕዝቡ የዴሞክራሲና የስልጣን ጥያቄ” በሚል ጉዳዩ በቀጥታ ስርጭት ሰፊ ተከታታይ ሽፋን እንዲያገኝ ያደርጋሉ፡፡ እነሱ የሕዝቡ የዴሞክራሲ ጥያቄ ተመለሰ የሚሉት፣ በዛ ሀገር ለእነሱ ብሔራዊ ጥቅም የማይበጀው መንግስት ወድቆ በምትኩ የእነሱ ተላላኪና ሎሌ የሀገሩን ብሄራዊ ጥቅም አሳልፎ ለምዕራባውያን የሚሰጥ ቡድን በወደ ስልጣን ሲመጣ ብቻ ነው፡፡

ለዚህም መሳካት በዚያች ሀገር ያለውን የመከላከያ ሰራዊት አመራር፣ የፖለቲካና የደህንነት ክፍሉን ጭምር ሰርገው በመግባት ወይንም በመደራደር “ከሕዝቡ ትግል ጎን መቆም አለባችሁ” በሚል ሽንገላ ያሰልፉታል። ግብፅን፣ ሊቢያን፣ ሶሪያን፣ የመንን ሌሎችንም ሃገራት እንዳልነበረ አድርገው ዛሬ ማጣፊያው አጥሮ ሁሉ ነገር እንዳልነበር ሁኖ ከተሞችና የሀገር ሀብት ወድሞ ተዘርፎ ሕዝቡም አለቆ የተረፈውም ተሰዶ ኢኮኖሚያቸውም ተንኮታኩቶ ያልታሰበና ያልተጠበቀው አክራሪነት ከመቸውም ግዜ በላይ አቅም አግኝቶ የተንሰራፋው፡፡

የኒዮ ሊበራሉ ቀኝ ክንድ የሆነው ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ በሽፋን እንደሚለው ለፍትሐዊ ነፃና ተዓማኒነት ላለው ምርጫ ለዴሞክራሲ ለሰብዓዊነት ለመልካም አስተዳደር መስፈን ወዘተ የቆመ አይደለም፡፡ የራሱን ሀገር ብሔራዊ ጥቅም ዓላማና የስትራቴጂ ፍላጎት በሌሎች ሀገራት ለማሳካት ይቻል ዘንድ ምርጫዎችን ሽፋን አድርጎ የራሱን ድብቅ አጀንዳ ይዞ ብዙ ሚሊየን ዶላር መድቦ ይንቀሳቀሳል፡፡ ቅጥረኛ ምሁራንና ተቃዋሚ ፖለቲከኞችን እየገዛና እየደለለ በራሳቸው ሀገር ላይ ያለጠመንጃ በብዕርና በፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በማሰለፍ መንግስት ጥሎ መንግስት ለመተካት የሚዘምት የሚያዘምት በአሜሪካ መንግስት ሙሉ ድጋፍ የሚደረገለት ስውር ሃይል ነው፡፡

አሳዛኙ ነገር የሌሎች ሀገራትና የእኛም ምሁራን ለየራሳቸው ሀገር የሚሆን የሚበጅ መፍትሔ ከሕዝባቸው ጋር ሆነው ማፍለቅ ማበጀት ሲችሉ፣ በውጭ ሀይሎች ድጋፍ እገዛ ጥገኝነት ስር ወድቀው መተማመናቸውና መኩራራታቸው ነው፡፡ ወሳኝ በሆነው ታሪክ ሰሪው ሕዝባቸው ሳይሆን በምእራቡ መንግስታት ተቋማትና ሀገራት በእጅጉ የሚኮሩ የሚተማመኑ አደግዳጊ ሎሌዎችና አሽከሮች መሆናቸው ነው፡፡

የራሳቸውን ሕዝብ ባህል፣ እምቅ አቅም የተፈጥሮ ፀጋ ይዘው በሕዝባቸውና በሕዝባቸው ብቻ ጸንተው በማንም የውጭ ሃይል ፖለቲካና ገንዘብ ሳይተማመኑ ጠንክረው ለሊት ከቀን የሰሩት እነቻይና፣ ኮሪያ፣ ሩሲያ፣ ሕንድ ብራዚል ወዘተ ከዛሬ 50 ዓመታት በፊት የነበሩበትን ድህነት ወደ ታሪክነት ለውጠው የዓለም የኢኮኖሚና የፖለቲካ ቁንጮ ወደመሆን እየገሰገሱ ነው፡፡ ያኔ ሀያል የነበሩት ምዕራባውያን የኒዮ ሊበራል ሀይሎች ደግሞ በኢንዱስትሪና በኢኮኖሚ ቀውስ እየታሹ እየወረዱም እየተነሱም በመንገታገት ላይ ናቸው፡፡

ከዚህ ቀውስ የሚታደጋቸው ድንግል መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ያላቸውን ሀገሮች እንደጥንቱ በቅኝገዢነት ማስገበር ስለማይችሉ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቀንበር ስር ጠልፈው ለመጣልና የኢኮኖሚ ቀውስ ችግራቸውን ለመታደግ ያላቸው ብቸኛ መፍትሔ በአዲሱ ቁመራቸው በተለያዩ ሀገራት በመለመሏቸው ቅጥረኛ ምሁራንና የፖለቲካ ተቃዋሚዎች አማካኝነት ሕዝቡን ለአመፅና ለሁከት ለትርምስ በማነሳሳት የራሳቸውን የፖለቲካና ኢኮኖሚ የሚያራምዱ ሀይሎችን ወደ ሀገር አመራር ፖለቲካ ስልጣን ለማምጣት ይሮጣሉ፡፡

ከተሳካላቸው የእነሱን ድንበር ተሻጋሪ ዓለም አቀፍ ገዙፍ ኮርፖሬሽኖች በብዛት ወደዚያች ሀገር በማስገባት በልማትና በኢንቨስትመንት ስም የሀገሪቱን ድንግል የተፈጥሮ ሀብት መመዝበር ዋነኛ ዓላማቸው ነው። ይህንን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሀገሬንና ሕዝቤን አላስመዘብርም አላዘርፍም የሚሉ መሪዎች ፓርቲዎች በኒዮ ሊበራል ሃይሉና በቅጥረኞቻቸው ዘመቻ ይከፈትባቸዋል፡፤

በተለያየ ስም ባቋቋሟቸው አምነስቲ ኢንተርናሽናል፣ ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ የፕሬስ ነፃነት ተሟጋች  ወዘተ በሚሉ ስሞች በሚንቀሳቀሱ ተቋማት ከፍተና የስም ማጥፋት ዘመቻ  ይካሄድባቸዋል፡፡ ታዛዣቸው ደግሞ ስማቸው ይወደሳል ፡፡

በተለያዩ ሀገራት የሀገሬው ሕዝብ እውነትም ለሰብዓዊነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለፍትሕ፣ ለመልካም አስተዳደር . . . የቆሙ እየመሰለው የተሻለ ሀገርና ቀን በመመኘት ‘ሆ’ ብሎ ድጋፉን የሰጠበት ብዙ አጋጣሚ ታየቷል። ይሁን እንጂ የተባለውና የተነገረው ባዶ ተስፋና ቃል  እንደቀትር ጤዛና ጉም በኖ ሲጠፋ ለመመልከት ሁለት ወርና ሶስት ወር እንኳን አልወሰደበትም፡፡

ሁሉም ነገር ከተጠበቀው ውጪ ሆኖ፣ በስርዓት አልበኝነት ተለውጦ፣ ሰላም ጠፍቶ ኑሮው ከበፊቱ በእጅጉ የከፋና አሰቃቂ ሁኔታ ውስጥ ወድቆ፣ የሚላስ የሚቀመስ ጠፍቶ “ምነው በቀረብን” ያሉበት ሁኔታ አለ። በአረቡም አለም በዩክሬንም ያጋጠመው በናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ ቅንብር የተመሩ የቀለም አብዮቶች ውጤት ነው፡፡

ገበያ አክራሪ ምእራባውያን የሕዝብ ታመስ፣ እልቂተ፣ ስደተ፣ የሃገር ውድመት፣ ምንም አያሳስባቸውም። ዋናው ጉዳያቸው ለባለፀጎቻቸው የሚመች ሁኔታ መፈጠሩ ነው። ይኼን ሁሉ አድርገው ሲያበቁ፣ “እናስታርቃለን፣ እንሸመግላለን፣ ለምግብና ለሕክምና አስቸኳይ እርዳታ፣ የመልሶ ማቋቋሚያ ፈንድ ይኸን ያህል ሚሊዮን ሰጥተናል” ይላሉ፡፡

በጎን ደግሞ የተለያዩ አንጃዎችን የጦር መሳሪያ ያስታጥቃሉ፡፡ ያሰለጥናሉ፡፡ ያዋጋሉ፡፡ ይሔ ሁሉ ቁማር ለራሳቸው ብሔራዊ ጥቅም መከበር ከዚያች ሀገር ሀብት ዘርፎ ለመክበር የሚያደርጉት ሩጫ እንጂ ለየትኛውም ሀገር ሕዝብ አስበውና ተጨንቀውም አይደለም፡፡እውነቱ እዚህ ድረስ ነው፡፡

ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ “እንደምን የኢትዮጵያ ጉዳይ አስጨንቆት አንድ ኢትዮጵያዊ ተቃዋሚ ምሁር ለ6 ወራት ቀጥሮ ስለዴሞክራሲ፣ በውጭ ስላለው ኢትዮጵያዊ ዲያስፖራ ተቃዋሚና በሀገር ውስጥ ስላለው ወይንም ስለሚኖረው ሚና ማስጠናት ፈለገ?” ብሎ ለሚጠይቅ ሰው መልሱ አጭርና ግልጽ ነው፡፡ መለሱ በእነሱ የሚደገፈውና የሚታዘዘው የሚመራው በዲያስፖራ የሚገኘው ፅንፈኛው የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት በተፈለገው መንገድ በሰላምም ሆነ በአመፅ የፖለቲካ ስልጣን እንዲይዝና ኢትዮጵያን እንዲመራ እንዲስተዳድር ማድረግ ነው።

ጥናቱ ያስፈለገበትም ምክንያት ተቃዋሚው በተደጋጋሚ ሽንፈትና ውድቀት ስላጋጠመው ከዚህ በመነሳት ጠንካራና ደካማ ጎኑን በመፈተሽ የምእራባውያንን ጥቅም በማስጠበቅ ዓላማው ድል አድራጊ የሚሆንበትን ስልትና ዘዴ ለመቀየስ ነው። ራሱን የፈተሸው ተቃዋሚው አይደለም። አለቆቹ ናቸው የፈተሹት፡፡ አሳፋሪውም ታሪክ ይሄ ነው ፡፡ የቀለም አብዮቱ የኋላ ደጀን ሁነው የሚመሩት እነ ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ የሚፈልጉትም በእነሱ የሚደገፈው ተቃዋሚ ውጤታማ እንዲሆን ነው፡፡

ዶ/ር መረራ ስለ ዲያስፖራው ጥናት ውጤት ሲገልጹ “ከዲያስፖራው ድጋፍ ውጪ ኢትዮጵያ ውስጥ መንቀሳቀስ ይከብዳል፡፡ አሁን ባለው የፖለቲካ ምህዳር ከሀገር ውስጥ የፋይናንስ ድጋፍ ማግኘት የሚቻልበት ደረጃ ላይ አይደለም፡፡ የዳያስፖራው ድጋፍ ያስፈልገናል፡፡ዳያስፖራው ግን ድጋፉን ሲሰጠን ውሀ ልኩን ካላወቀ ሀገር ውስጥ የሚደረገው ትግል መልኩን ሊስት ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገውን ሰላማዊና ሕጋዊ ትግል ዳያስፖራው በውጭ ደረጃና ሚዛን ካየው እንዲሁም እንደዚያ ተንቀሳቀሱ ካለ አገር ውስጥ በዚያ ደረጃ መንቀሳቀስ ስለማይቻል ብዙ የተስፋ መቁረጥ ዝንባሌ ይከሰታል፡፡” ብለዋል።

ሌላው ዳያስፖራ በሚሰጠው ድጋፍ መጠን በሚፈልገው አቅጣጫ ግፋበት የማለት ዝንባሌ ይታያል፡፡እዚህ ላይ ዶ/ር መረራ ጥሬ እውነቱን በትክክል አስቀምጠውታል፡፡ ዳያስፖራው ድጋፉን ሲሰጥ “እኔ ያልኳቸውን ፈፅሙ፣ አድርጉ” ማለቱ አይቀሬ ነው። ይህ ደግሞ አቶ ይልቃል ጌትነት እየዳከረበት እንደሚገኘው ሁኔታ ራሱን የቻለ ችግር ሊያመጣ ይችላል፡፡

አብዛኛው ዳያስፖራ የሀገሩን ሰላምና እድገት ፈላጊ ሲሆን ሰርቶም ወደ ሀገሩ ለቤተሰቡ ገንዘብ በመላክ የሚረዳ ነው፡፡ ከፖለቲካ እንቅስቃሴም ውጪ ነው፡፡ ጥቂትና አክራሪ ፅንፈኛ ተቃዋሚ የዲያስፖራ ፖለቲከኞች ደግሞ የተቃውሞ ፖለቲካን ገንዘብ መሰብሰቢያ የራሳቸውን ኑሮ መኖሪያ አድርገውታል፡፡ ጽንፈኛው ተቃዋሚ ዳያስፖራ እያስፈራራ ወይንም ባዶ ተስፋና ቃል እየመገበ፣ የማይችለውን አደርጋለሁ እያለ በንጹህ ላቡ ሰርቶ ከሚኖረው ኢትዮጵያዊ ዳያስፖራ በመዋጮ የሚሰበሰበው ውስን ነው፡፡ ዋናው የገንዘብ ምንጩ የኒዮ ሊበራል ሃይሎች ናቸው።

ሌሎችም የገንዘብ ምንጮች አሉት፡ ፡ከኩዌትና ከግብጽ ለኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች የተመደበው ገንዘብ በሻዕቢያ አማካይነት ይደርሰዋል፡፡ እነዚህ ሁሉ ከተለያዩ ምንጮች የሚጫኑ ገንዘቦች ናቸው ወደ ሀገር ቤቱ ተቃዋሚ ከዳያስፖራው አክራሪ ሀይል በተለያየ መንገድ እንዲገቡ የሚደረገው። የሀገር ቤቱ ተቃዋሚ እንቅስቃሴው በዳያስፖራው ገንዘብ ብቻ የሚተማመን ከሆነ ጥገኛና ነፃነት የሌለው የእነሱን አጀንዳ አስፈጻሚ ብቻ ነው የሚሆነው። አሁን ያለውም እውነት ይኸው ነው፡፡

ተቃዋሚው የተፍረከረከ የተበታተነ፣ ከውጭ ገንዘብ ሲመጣ ለመቀራመት እንደ ጅብ እያስካካ የሚሰባሰብና ተቀራምቶ የሚበላ፣ ያጣ ለታ ደግሞ እርስ በእርሱ የሚባላ ነው። በየትኛውም መስፈርት በፖለቲካ ተወዳድሮ ብቁ ሁኖ ለማሸነፍ የማይበቃ ግርግርና ትርምስ እየፈጠረ መግለጫ እያወጣ እየተንጫጫ የሚኖር ለየትኛውም ኃላፊነት የማይበቃ ጥገኛ ነው፡፡

ዶ/ር መረራ እንዳሉት "ዳያስፖራው ሀገር ቤት ካለውም በበለጠ ከሁሉም በላይ አስቸጋሪው በብሔር መከፋፈሉ ነው፡፡ ምን ዓይነት ለውጥ መምጣት አለበት በሚለው ላይ ሀገር ቤት ያለውም ዳያስፖራውም ስምምነት ላይ ካልደረሰ የሚደረገውን ትግል ለመግፋት ይቸግራል ይሄም ትልቅ እውነት ነው፡፡ ዳያስፖራው በፖለቲካው ብቻ ሳይሆን በሀይማኖትም ጭምር መከፋፈል ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ በፖለቲካው ክፍፍል በተለይ በብሔረሰብ ጥያቄ ዙሪያ ሁለት ፅንፍ አለ፡፡ መሀል መንገድ ላይ የሚሰባሰቡ ሀይሎች ተፈጥረው የኢትዮጵያን እጣ ፈንታ ሊወስን የሚችል ዴሞክራሲያዊ ትግል መልክ ማስያዝ እስካልቻለ ድረስ ያለማጋነን የሁለት ፅንፎች እስረኛ እንሆናለን።" ይላሉ።

ዶር መረራ አያይዘው፣ "አንዱ ኢትዮጵያ የሚባል ነገር አልሰማም ይላል፡፡ሌላው ደግሞ የኢትዮጵያዊነት ሰርተፍኬት ሰጪም ከልካይም እኛ ነን ይላል፡፡ ኢትዮጵያ በሀገር ደረጃ ያለባት ችግር ይሄን ፈተና የማሸነፍና ያለማሸነፍ ነው፡፡ በአጠቃላይ ትግሉ ተጎድቷል፡፡ ክርር ወዳለው መስመር መሰባሰብ አለ፡፡አብዛኛው ሰውም በዚህ ሀይል ስር ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ ገዢው ፓርቲ የፖለቲካ ምህዳሩን በማጥበቡ ነው።"

ዶ/ር መረራ የተናገሩት አብዛኛው ደረቅ እውነት ነው፡፡ ጽንፈኛው ዳያስፖራ በፅንፍ የተከፋፈለ ስለሆነ ለራሱም ለሀገሩም አይበጅም፡፡ ዛሬም መከፋፈሉ ቀጥሏል፡፡ ወደፊትም መቼም አይቆምም፡፡